**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!**

# ኦሪት ዘፍጥረት 11:7 እና ምስጢረ ሥላሴ

**ጉልላት አበበ**

በዚህ ፅሁፍ በዘፍጥረት ምዕራፍ *11* ቁጥር *7* ላይ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል በማንሳት ቃሉ እንዴት ሥላሴን ሊያሳይ እንደሚችል እናያለን።

> **ኦሪት ዘፍጥረት 11:7**
>
> **"ኑ፥ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።"**

## 1. ኑ ÷ እንውረድ

ይህንን ክፍል የምናብራራው ከእግዚአብሔር ማንነት በመነሳት ሲሆን እግዚአብሔር "ኑ : እንውረድ" እያለ ያለው ማንን ነው የሚለውን እናያለን። በመጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ነገሮችን ለመፈፀም እገዛ ይሻል ወይም የሌላ አካል እገዛ ወይም ምክር ይጠብቃል? የሚለውን ማየት ጠቃሚ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድን ነገር ለመፈፀም የሌላ አካል እርዳታ እንደማያስፈልገው በግልጽ ተቀምጧል፡-

- **ትንቢተ ዳንኤል 4:35** — "በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም፦ ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።"
- **ትንቢተ ኢሳይያስ 40:13-14** — "የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፥ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?"
- **የሐዋርያት ሥራ 17:25** — "እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።"

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መሰረት እግዚአብሔር ሥራውን ለመሥራት አጋዥ ወይም አማካሪ አያሻውም። ከዚህ በመነሳት እኛ ክርስቲያኖች እንዲህ ብለን እንጠይቃለን፦ እግዚአብሔር ለሥራው ሌላ አካል (መላእክት ወይም ሌላ ፍጡር) የማያሻው ከሆነ ማንን ነው "ኑ : እንውረድ" ያለው?

መልሱንም አባታችን ቅዱስ የሐንስ አፈወርቅ እንዲህ በማለት ይመልሱታል፡-

> *"Let us go down.' This remark, however, is made as if to those of equal status:"*
> ይህም ማለት ተናጋሪው አካል ሌላ ከእርሱ ጋር እኩል የሆነ አካላትን እያነሳ ነው፤ ይኸውም በግልጽ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን መሆኑን ያሳየናል።

## 2. አውድ (Context)

የክፍሉን አውድ ስንመለከት፦

- **ኦሪት ዘፍጥረት 11:5** — "እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ።"
  *(የወረደው ማነው? እግዚአብሔር - ነጠላ ቁጥር)*
- **ኦሪት ዘፍጥረት 11:8** — "እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው፤ ከተማይቱንም መሥራት ተዉ።"
  *(በምድር ሁሉ ላይ የበተናቸው ማነው? እግዚአብሔር - ነጠላ ቁጥር)*
- **ኦሪት ዘፍጥረት 11:7** — "ኑ፥ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።"

ስለዚህ በአውዱ መሰረት «ኑ : እንውረድ» የተባሉት አካላት «ወረደ» ከተባለው እና «ቋንቋውን ካደባለቀው» ከአንዱ እግዚአብሔር ጋር አንድ ናቸው። ስለዚህ የብዙ ቁጥሩ አገላለጽ (ንግግር) የራሱ የዚያው የአንዱ እግዚአብሔር እንጂ የሌሎች የተፈጠሩ ፍጡራን አይደለም።

**ትክክለኛው የታሪኩ ፍሰት፦ Humanity rebels → God observes their pride → God judges them → God scatters them.**

ከአውዱ የምናየው ነገር ሙሉ በሙሉ የድርጊቱ አካል እግዚአብሔር እንጂ መላእክትን አይደለም። ስለዚህ የሙሉ የታሪኩ ፍሰት፣ የድርጊቱ ባለቤት እግዚአብሔር ከሆነ "ኑ ፥ እንውረድ" የተባሉት አካላት እግዚአብሔር ናቸው ማለት ነው። ይህም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ!

## 3. ሙስሊሞች እና ሌሎች አሐዳውያን የሚያነሷቸው ሙግቶች እና መልሶቻቸው

### ሙግት 1፦ God speaking to His heavenly court (the angels)

ይህ በብዙሃኑ አሐዳውያን የሚነሳ ሙግት ሲሆን እግዚአብሔር "ኑ እንውረድ" ሲል እየተናገረ ያለው ለመላእክት ነው የሚል ነው። ይኸውም "ኑ እንውረድ" የሚለውን የብዙ ቁጥር አገላለጽ ለመላእክት ይሰጡና የድርጊቱ ፈጻሚ ግን ራሱ እግዚአብሔር ነው ይላሉ። ምክንያታቸው ደግሞ ድርጊት ገላጩ ግስ ነጠላ (singular) ነው የሚል ሙግት አላቸው። በዚህም በሥራው አላሳተፋቸውም ግን ነገሯቸዋል ይላሉ፦

Genesis 11:7: "Let us go down..." (plural) | Genesis 11:8: "The LORD scattered them..." (singular)

ለዚህም ሀሳባቸው የሚያነሱት ጥቅስ፦ **1 ነገሥት 22:19-20** "...እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ፥ የሰማይም ሠራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው አየሁ..."

**የክርስቲያኖች መልስ፦**

**ሀ) የድርጊቱ ፈጻሚ እግዚአብሔር ነው። መላእክት ቋንቋቸውን አልደባለቁም!**
ዘፍጥረት 11:7 ላይ "ኑ እንውረድ... ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው" ካለ በኋላ ድርጊቱ ላይ ግን በግልጽ እግዚአብሔር ይላል (ዘፍጥረት 11:8)።
*Christian argument: If God was speaking to angels, why are they never said to participate?*
ስለዚህ "ኑ እንውረድ" እያለ ያለው ድርጊቱን ለሚፈጽመው እኩል ለሆነ አካል ነው።

**ለ) የመላእክት ስም አልተነሳም!**
ይህ አርጉመንት ለምን ይሰራል ከተባለ አሐዳውያን ፈጣሪ መላእክትን ያናግራል ብለው የሚያመጧቸው ጥቅሶች ውስጥ በግልጽ "መላእክት" ወይም "የእግዚአብሔር ሠራዊት" ተብሎ ተጠቅሷል። በዚህ ክፍል ላይ ግን መላእክት ለማለት የሚያስችል ምንም ፍንጭ የለም!!
*Christian argument: Reading angels into Genesis 11:7 requires bringing in an idea from other passages rather than from the text itself.*

**ሐ) ፈጣሪ ለሥራው ረዳትን ወይም አማካሪን አይፈልግም!**
በኢሳይያስ 40:13 ላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር አማካሪ የለውም።
*Christian argument: If God needs no helpers, why would He invite angels to participate in His judgment?*

### መግት 2፦ Argument : Plural of Majesty (የግርማዊነት ብዙ ቁጥር)

ይህንን የሚያነሱ አሐዳውያን፦ አንድ ንጉሥ ወይም ገዥ ባለሥልጣንነቱን፣ ግርማዊነቱን ወይም ክብሩን ለመግለጽ ከ"እኔ" ይልቅ "እኛ" በማለት ስለራሱ ሊናገር ይችላል ይላሉ።

**ይህንን መከራከሪያ በቀላሉ ማፍረስ ይቻላል፦**

- በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕብራይስጥ ቋንቋ እግዚአብሔር ስለ ራሱ ለመናገር የግርማዊነት ብዙ ቁጥርን (Royal Plural) ስለመጠቀሙ ግልጽ የሆነ ምሳሌ የለም።
- "የንግሥና እኛ" (Royal We) በአንዳንድ የኋላ ኋላ ቋንቋዎች ዘንድ በሰፊው የሚታወቅ ቢሆንም፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕብራይስጥ ውስጥ ያለው አገልግሎት አሁንም አከራካሪ ነው።
- እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረው በነጠላ ቁጥር ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ በሙሉም እግዚአብሔር በተደጋጋሚ እንዲህ ይላል፦
  - "ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ..." (ዘፍጥረት 17:2)
  - "እኔ ኤልሻዳይ (ሁሉን ቻይ አምላክ) ነኝ..." (ዘፍጥረት 17:1)
  - "እባርክሃለሁም..." (ዘፍጥረት 12:2)
- እግዚአብሔር በልማድ የግርማዊነት ብዙ ቁጥርን የሚጠቀም ቢሆን ኖሮ፣ ይበልጥ በተደጋጋሚ ሲገለገልበት እንመለከት ነበር በማለት የቋንቋው ምሁራን ይገልጻሉ።

## 4. የቤተክርስቲያን አባቶች ትምህርት

### ኖቫቲያን (Novatian - On the Trinity 17.7)

በዘፍጥረት 11:5 «እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ።» በሚለው ላይ፦ የወረደው አካል "እግዚአብሔር" ተብሎ ነው የተጠራው እንጂ መልአክ ተብሎ አይደለም። በመሆኑም የወረደው መልአክ አይደለም። መላእክት በዚህ የጽሑፍ ክፍል እንደ እግዚአብሔር ሆነው አይነገሩም፤ ጸሐፉ ፍርዱን በቀጥታ ለራሱ ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

በተጨማሪም የወረደው አብ አይደለም። ኖቫቲያን ሲያስረዳ፤ አብ የማይታይ ነው፤ እንዲሁም በዓለም ላይ በግልጽ (በመገለጥ) የሚታየው አካል እርሱ አይደለም። ስለዚህ፣ የወረደው ወልድ (ቃል/Logos) ነው። እግዚአብሔርን ለሰው ልጅ የሚገልጠው ወልድ ነው። ኖቫቲያን ይህንን ሀሳብ ክርስቶስን ከሚያመላክተው ከኤፌሶን 4:10 ጋር ያያይዘዋል፦ “ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።”

### ቅዱስ አውግስጢኖስ (St. Augustine)

አውግስጢኖስ ሁለት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጓሜዎችን ያቀርባል፦

1. አንደኛው ሊሆን የሚችል ትርጓሜ እግዚአብሔር በመላእክቱ አማካኝነት "ወረደ" የሚለው ነው።
2. ሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ የሚለው ነው። ለዚህም ምክንያቱ መላእክት በተፈጥሯቸው ወዲያውኑ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሚንቀሳቀሱ "ኑ" ተብለው መጠራት አያስፈልጋቸውም የሚል ነው።

**ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (St. John Chrysostom)**

*"This remark... is made as if to those of equal status"*

“ኑ : እንውረድ“ ማለቱ እኩል ማዕረግ ላላቸው አካላት የተነገረ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ እርዳታን አይፈልግምና። ዮሐንስ እንደሚያስረዳው፤ እነዚህ ቃላት ለአገልጋይ ወይም ዝቅተኛ ማዕረግ ላለው አካል ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር እኩል ከሆነ ሌላ አካል ጋር እንደሚነጋገር ያሳየናል፤ ይኸውም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው።